በስልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ዜጎቹን ከጥቃት ሊከላከል ስለማይችል ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ጥሪ ቀረበ።






በየመን ፣በደቡብ አፍሪካ እና በሊቢያ ውስጥ ባሉ ኢትዮጵያን ላይ የተፈፀመውን መጠን የለሽ ግፍ በማውገዝ ኢትዮጵያውያን በኖርዌ ሰልፍ ወጡ።

ሰልፉ የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ስደተኞች ማሕበር በኖርዌይ አስተባባሪነት ሲሆን ሁለት ዓይነት ዓላማዎች ነበሩት ይኸውም፥

1ኛው:- ሐገራት ዜጐቻቸውን ከየመን ጦርነት ሊያሸሹ ትራንስፖርት ለመላክ ከላይ እታች ሲሉ ኢትዮጵያንን እወክላለሁ ብሎ የሚቀባጥረው ወያኔ ስልክ ደውሉ ሲል ማሾፋውን፤በሊብያ አይሲሲ ኢትዮጵያውያንን አረድኩ ብሎ እየተናገርና የዓለም መነጋገሪያ ሆኖ እነ አሜሪካ የሐዘን መግለጫ እየላኩ ባለበት ወቅት ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ለማጣራት እየሞከርኩ ነው ብሎ የተሳለቀውን ፤ በደቡብ አፍሪካ ከነሕይወታቸው በእሳት ሲቃጠሉ እንደሐገር መሪ ይሕ ነው የሚባል መልስ ያልሰጠውን ወያኔ ለማውገዝ እና

2ኛ:- ኢትዮጵያውያንን ከውርደትና ከጥቃት ሊከላከል የሚችል ለኢትዮጵያውያን የቆመ መንግስት በኢትዮጵያ ስለሌለ በሊቢያ፣በየመን፣በደቡብ አፍሪካ በሞት አፋፍ ላይ ያሉትን ኢትዮጵያዉያንን ሕይወት የዓለም መንግስታት እንዲታደጉ ጥሪ ለማድረግ ሲሆን ፤የሐገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ስሜትና መሪር ሐዘን የተገለፀበት፤የወገን ተቆርቋሪነት የታየበት ነበር።

በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ላለው መከራና ስቃይ ሁሉ ተጠያቂው ወያኔ

የተባለው፤ከትግራይ ነፃ አውጭነት ስሙን እንኩዋን መቀየር ሳይችል 24 ዓመት በሙሉ በኢትዮያውያን ጫንቃ ላይ ተቀምጦ ኢትዮድያን እያፈረሰና ሕዝብ እየጨፈጨፈ ያለውና እራሱን መንግስት ነኝ ብሎ የሚቆጥረው የወያኔ ቡድን በመሆኑ   እንደዜጋ ተከብሮ ለመኖር ወያኔን ለመጣል የእያንዳንዱ ኢትዮድያዊ የትግል አስተዋፆ ወሳኝ እንደሆነ ገልፀው በየመን ፤በሐገር ቤት በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ ባሉ ኢትዮድያውያን ወገኖቻቸው ላይ የተፈፀመውን ግፍ በመቃወም የተሰማቸውን መሪር ሐዘን ለመግለፅ ሰልፍ በወጡት ኢትዮድያውያን ላይ በወያኔ የደረሰውን ድብደባና እስር በማውገዝ የኢትዮድያው አይ ሲ ሲ ሲሉ ገልፀውታል።

ምቹ ሕይወቱን ትቶ ለኢትዮድያ ሕዝብ ነፃነት፣ ፍተሕና እኩልነት የታገለውን የኢትዮድያ ማንዴላ አንዳርጋቸውን ለእኩይ ተግባሩ ፕሌን የላከው ወያኔ በየመን በሙቶ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮድያንን ከጦርነት ለመታደግ ያልምከረው ለሕዝብ ዴንታ ስለሌለዉ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም ሰልፈኞቹ በመፈክራቸው የዓለም መንግስታት ኢትዮጵያውያንን በማሸበር ላይ ያለውን ወያኔ ከመርዳት እንዲታቀቡ ያሳሰቡ ሲሆን በተጨማሪም፤

አለማቀፉ ሕብረተሰብ በሊብያ፣ በየመን እና በደቡብ አፍሪካ ችግር ውስጥ ላሉ ኢትዮድያውያን እንዲደርስላቸውና በኖርዌ ያሉ ኢትዮድያውያን ስደተኞችን ጉዳይ የኖርዌ መንግስት ባግባቡ እንዲያይ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለኖርውጃን ፓርላማ ከተሰጠ በሁዋላ

በሰልፉ ላይ የተለያዩ ድርጅት ተወካዮች ንግር ያደረጉ ሲሆን ዶክተር ሙሉ ዓለም፣ የዲሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮድያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ ም፡፡ሊ አቶ ዳንኤል አበበ፣ የአዲስ ቃል ኪዳን ፈውስ አገልግሎት ሚኒስትሪ አገልጋይ ወ፡፡ሮ ሰዋሰው ስለሺ አቶ ሐሰን መሐመድን ይዘው እኛ የኢትዮድያውያን ሙስሊሞችን እና ክርስቲያኖችን ወክለን አብረን ቆመን እንፀልያለን ፤በኢትዮድያ ሙስሊምና ክርስቲያኖች መካከል ምንም ችግር የለብንም ፤አይ ሲ ሲ የኢትዮድያን ሙስሊም አይወክልም እኛ አንድ ነን ብለው ከሰልፈኛው ጋር በኖርውጃውያን ፓርላማ ፊት ለፊት ተንበርክከው ወደፈጣሪያቸው አቤት ያሉ ሲሆን እግዚአብሄር ግፈኞችን እንዲያስወግድ ተማፅነው ፤የእምነት ሰዎች ነን እያሉ እውነቱን በመደበቅ በእግዚአብሄር እየነገዱ ያሉትም የእምነት ሰወች ተወቅሰዋል። ሰልፈኞቹም በወገኖቻቸው ላይ በደረሰው ግፍ የተሰማቸውን መሪር ሐዘን በለቅሶ ሲገልፁ ታይተዋል።

ዘወትር በሐገራቸው ጉዳይ ላይ ወደሁዋላ የማይሉት አቶ አምሳል ካሴም ፪፬ ዓመት ኢትዮድያን እያወደመ ያለውን ወያኔ ከስልጣን ለማስወገድ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት፤ በሐገር ቤትም በውጭም ኢትዮድያውያን እየተጨፈጨፉ

የችግራችን ምንጭ የሆነውን ወያኔ ለመጣል የማይነሳ ሁሉ ተጠያቂ እንደሆነ አስጠንቅቀዋል።

የኢትዮድያ ስደተኞች ማሕበር በኖርዌም በሰልፉ ላይ የተገኙትን በሙሉ አመስግኖ ዘወትር

ማሕበሩ በሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ከጐኑ በመቆም ታላቅ አስተዋፆ እያበረከቱ ያሉትን አቶ ዩሐንስ አበራን ከልብ አመስግኗል ።

የኢትዮጲያ ስደተግኛ ማህበር በኖርዌ

ዮናስ ታምሩ

ህዝብ ግኑኝነት